# የሜዳይ፣ ኒሻን እና ሽልማት ረቂቅ አዋጅ አጭር ማብራርያ

ታህሳስ 2016 ዓ.ም.

## 1. መግቢያ

ማንኛውም ሀገር ከፍተኛ ወይም የላቀ ስኬት እና ስራ ላስመዘገቡ ዜጎቻቸው ዕውቅናና ሽልማት የሚሰጡበት ስርዓት አለው፡፡ ይህ አይነት ሽልማት ዜጎች በተሰማሩበት የስራ ዘርፍ ለሀገር የሚያደርጉት የላቀ አስተዋጽኦ አገር ባለዉለታ አድርጋ እንደምታከብራቸዉ እና ይህም በየተተኪዉ ትዉልድ መነሳሳትን የሚፈጥር ተግባር ነዉ፡፡ የአብዛኛዉ አገራት ልምድ እንደሚያሳየን የላቀ ስኬት ላስመዘገቡ ግለሰቦች እና ድርጅቶች እዉቅና የሚሰጠዉ ሜዳይ ወይም ኒሻን በመሸለም ነዉ፡፡ ሜዳይ እና ኒሻን ማለት ለተለየ ኩነት ወይም ለላቀ ውጤት እውቅና ለመስጠት በአብዛኛው ሳንቲም በሚመስል ብረት ላይ ጌጥ በመቅረጽ ወይም በማተም፣ የማዕረግ አርማ በማድረግ ወይም ቃላትን፣ ድርጊትን ወይም ኩነትን በሚገልጽ መልኩ በመቅረጽ በተለያዩ ዘርፎች የላቀ ውጤት ላስመዘገቡ ሰዎች የሚሰጥ የክብር ሽልማት ነው::

በሀገራችንም የእነዚህ ሜዳይ እና ኒሻን ሽልማቶች ታሪክ ስንመለከት በቀደምት ግዜ ከአጼ ዮሀንስ ዘመነ መንግስት ጀምሮ የሜዳይ ሽልማቶችን የመስጠት ልምድ የነበረ ቢሆንም በአጼ ሀ/ስላሴ ዘመን ጀምሮ በህግ ደረጃ ሜዳዮች ተቋቁመዉ ሲሸለሙ ቆይተዋል፡፡ በአጼ ሀ/ስላሴ ዘመን የአርበኞች ሜዳይ፤ የዉስጥ አርበኞች ሜዳይ፣ የስደተኞች ሜዳይ፤ የቀዳማዊ ሀ/ስላሴ የጦር ሜዳይ፤ የቀዳማዊ ሀ/ስላሴ የብሔራዊ አገልግሎት ሜዳይ እና ሌሎች ሜዳዮች የተቋቋሙ ሲሆን በደርግ ዘመን ደግሞ የጦር ሜዳ ሜዳዮችና አርማ፤ የሥራና አገልግሎት ሜዳዮች፤ የከፍተኛ ዉትድርና አገልግሎት ሜዳዮች እና የተለያየ ደረጃ ያላቸዉ ኒሻኖች እና ሽልማቶች ተቋቁመዋል፡፡

በመቀጠል ለመጀመርያ ግዜ በኢፌድሪ ህገ-መንገስት ሜዳይ፣ ኒሻን እና ሽልማቶች በሀገሪቱ ፕሬዝዳንት እንደሚበረከቱ ተደንግጓል፡፡ ይሁንና ይህ ህገ-መንግስት ከወጣ በኋላ ቁጥራቸዉ አነስተኛ የሆነ የምስክር ወረቀቶች፣ ሜዳዮች እና ኒሻኖች ለኢትዮጵያዉያን እና ለዉጭ ሀገር ዜጎች የተበረከተ ቢሆንም በህገ-መንግስቱ የተቀመጠዉን ሜዳይ፣ ኒሻን እና ሽልማት አሰጣጥን ወደ ተግባር የሚያወርድ የህግ ማዕቀፍ አልተዘረጋም ወይም ይህን የሚመራ ህግ እስካሁን አልወጣም፡፡

DANIEL FIKADU LAW OFFICE

በመሆኑም በሀገራችን እና አህጉራችን በፖለቲካ፣ ኢኮኖሚ፣ ማበራዊ እና ሌሎች ዘርፎች የላቀ አስተዋጽኦ ያበረከቱ እና ሀገራዊ እዉቅና እና ሽልማት ሊሰጣቸዉ የሚገቡ ግለሰቦች እና ድርጅቶች ያሉ ቢሆንም ይህን ማስፈጸም የሚያስችል ህግ ባለመዉጣቱ ምክንያት ለግለሰቦቹ እና ድርጅቶቹ ተገቢዉ እዉቅና ሳይሰጥ ቆይቷል፡፡ ስለሆነም ሀገራችን ባለዉለታዎቿን ክብር በመስጠት ቀጣይ ትዉልድ በተሰማራበት የስራ ዘርፍ ተግቶ በመስራት ለክብር ለመብቃት የሚነሳሳበትን ሁኔታ በህጋዊ ስርዓት መዘርጋት ስለሚያስፈልግ ይህን የሜዳይ፣ ኒሻን እና ሽልማት ረቂቅ አዋጅ ተዘጋጅቷል፡፡

## 2. የአዋጁ ዓላማ

ይህን አዋጅ ማዉጣት ያስፈለገበት ዓላማ፡-

1. በሀገሪቱ ብሎም በአፍሪካ ወይም ዓለም አቀፍ ደረጃ በተለያየ ዘርፎች ለሀገር እና ህዝብ እንዲሁም በአጠቃላይ ለሰዉ ልጆች የሚጠቅም የላቀ ተግባር የፈጸሙ ሰዎችን ወይም አካላትን እዉቅና በመስጠት ሌሎች የእነሱን አርአያነት እንዲከተሉ ማድረግ፤

2. በህገ-መንግሰቱ መሰረት ማስፈጸሚያ አዋጅ ሳይወጣላቸዉ እየተሰጡ ያሉ የተለያዩ ሽልማቶችን ወጥ የሆነ ህጋዊ የአሰራር ስርዓት እንዲኖረዉ ለማስቻል ነዉ፡፡

## 3. አዋጁን የማርቀቅ ሂደት

ይህን አዋጅ በማዘጋጀት ሂደት አዋጁን ለማዘጋጀት ያለዉን ህገ-መንግስታዊ መሰረት ለመዳሰስ ጥረት ተደርጓል፡፡ በኢፌድሪ ህገ-መንግስት አንቀጽ 71(5) እና 74(10) ላይ በተደነገገዉ መሰረት የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በሚያወጣው ህግ ወይም ውሳኔ መሰረት ኒሻኖችን እና ሽልማቶችን ጠቅላይ ሚኒስትሩ ለፕሬዝዳንቱ አቅርቦ እንደሚያሰጥ፤ እንዲሁም የሀገሪቱ ፕሬዝዳንት ኒሻኖች እና ሽልማቶችን እንደሚሰጥ ተደንግጓል፡፡ ከእነዚህ ድንጋጌዎች መረዳት የሚቻለዉ የሜዳይ፣ ኒሻን እና ሽልማት አሰጣጥን የሚመራ ህግ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በቅድሚ እንዲያወጣ ሀላፊነት የተሰጠዉ መሆኑን እና እነዚህ ህገ-መንግስታዊ ድንጋጌዎች ይህን አዋጅ ለማዉጣት የህግ መሰረት እንደሆኑ መገንዘብ ተችሏል፡፡

DANIEL FIKADU LAW OFFICE

በተጨማሪም በሜዳይ እና ኒሻን አሰጣጥ የተሻለ የህግ ስርዓት ያላቸዉን፤ እንዲሁም የመንግስት ስርዓታቸዉ ከሀገራችን የፌደራሊዝም ስረዓት ጋር ተመሳሳይ የሆኑ እንደ ናይጄሪያ፣ አሜሪካ እና ሌሎች ሀገራትን ልምድ ለመዳሰስ እና በጉዳዩ ዙርያ የተከናወኑ ጥናቶችን ለማየት ተሞክሯል፡፡

## 4. <u>የረቂቅ አዋጁ ይዘት</u>

ረቂቅ አዋጁ በአምስት ክፍሎች እና በ29 አንቀጾች የተዋቀረ ሲሆን በክፍል አንድ ስር የአዋጁ አጭር ርዕስ፣ ትርጉም እና ተፈጻሚነት ወሰንን የተመለከቱ ድንጋጌዎች ተቀምጠዋል፡፡ የአዋጁን ተፈጻሚነት ወሰንን በተመለከተ ረቂቅ አዋጁ በብሄራዊ ዉትድርና አገልግሎት ወይም በፖሊሳዊ አገልግሎት ዘርፍ ካሉት በስተቀር በዚህ አዋጅ መሰረት ሜዳይ፣ ኒሻን እና ሽልማት ለመሸለም ብቁ በሆኑ ወይም በተሸለሙ ማንናቸዉም ግለሰቦች፣ ቡድኖች እና ድርጅቶች ላይ ተፈጻሚ እንዲሆን ታስቧል፡፡ በወታደራዊ እና ፖሊሳዊ ዘርፍ ያሉ አካላት ሜዳይ እና ሽልማት አሰጣጥን በተመለከተ በብሔራዊ ዉትድርና አገልግሎት አዋጅ እና በፌደራል ፖሊስ አባላት መተዳደርያ ደንብ ቁጥር 268/2005 ዉስጥ የተሸፈነ በመሆኑ ይህ አዋጅ ከዉትድርና እና ፖሊስ አገልግሎት ዉጪ ያሉ አካላት ላይ ብቻ ተፈጻሚ እንዲሆን ተደርጓል፡፡

በረቂቅ አዋጁ ክፍል ሁለት በዚህ አዋጅ የተቋቋሙ ሜዳዮች እና ኒሻኖች ምንነት እና የሚያስገኙት መብቶችን የተመለከቱ ድንጋጌዎች ተካተዋል፡፡ ሜዳዮችን በተመለከተ በዚህ ረቂቅ አዋጅ አንቀጽ 4 ስር **ብሔራዊ የላቀ የፈጠራ ስራ ሜዳይ፣ ብሔራዊ የህዳሴ ሜዳይ** እና **ብሔራዊ የላቀ ሲቪል አገልግሎት ሜዳይ** እንዲቋቋሙ ተደርጓል፡፡

**ብሔራዊ የላቀ የፈጠራ ስራ ሜዳይ** በሀገር አቀፍ ወይም በዓለም አቀፍ ደረጃ በኢኮኖሚዊ ወይም በማህበራዊ ዘርፍ የላቀ የህብረተሰብን ችግር ሊፈታ ወይም ለሚፈታ የፈጠራ ስራ የሚሰጥ ሽልማት ሲሆን ይህ የፈጠራ ስራ በግለሰቦች፣ በቡድን ወይም በድርጅት የተሰራ የፈጠራ ስራ ሊሆን ይችላል፡፡ እንዲሁም በየግዜዉ የሚወጡ እጅግ ብዙ የፈጠራ ስራ ዉጤቶች ያሉ በመሆኑ እና ሁሉንም እዉቅና መስጠት የማይቻል በመሆኑ አንድ የፈጠራ ስራ የሰራ ሰዉ በዚህ አዋጅ ሜዳይ ሊሸለም የሚችለዉ በዚህ ረቂቅ አዋጅ አንቀጽ 2(1) ላይ እንደተመለከተዉ የፈጠራ ስራዉ በሀገሪቱ አግባብነት ባላቸዉ የፓተንት ወይም

የቅጂና ተዛማጅ መብት ህጎች መሰረት ፓተንት ወይም የቅጂ መብት የተሰጠዉ መሆኑ አስፈላጊ በመሆኑ ይኸዉ ተደንግጓል፡፡

በተመሳሳይ በአንቀጽ 6 ላይ በሳይንስና ምርምር፣ በቴክኖሎጂ፣ በስነ-ጥበብ ፣ስፖርት ወይም በተለያዩ ዘርፎች የላቀ ስራ ለሰሩ ግለሰቦች፣ ቡድኖች እና ድርጅቶች **የብሔራዊ የህዳሴ ሜዳይ የሚሸለሙ ይሆናል፡፡**

በሌላ በኩል በመንግስት መርስያ ቤት የሚሰሩ ሰራተኞች ለረጅም ግዜ አርአያነት ያለዉ አገልግሎት ሰጥተዉ በጡረታ ወይም በሌላ ምክንያት መስሪያ ቤቱን ከለቀቁ በኋላ ወይም በስራ ላይ እያሉም ቢሆን የሚታወሱበት ወይም የፈጸሙት አገርን በአሪያነት የማገልገል ተግባር እንደሀገር እዉቅና እና ክብር የሚሰጥበት ስርዓት ያልነበረ በመሆኑ እና በመንግስት ሰራተኞች ዘንድ ቀጣይ ተነሳሽነት እንዲፈጠር ለማድረግ የስራ ዲሲፕሊን ጠብቀዉ በታታሪነት እና በታማኝነት በማገልገል የላቀ ስራ ለሰሩ የመንግሰት ሰራተኞች የሚሸለሙት የሜዳይ ሽልማት አይነት ማቋቋም ስላስፈለገ **የብሔራዊ የላቀ ሲቪል አገልግሎት ሜዳይ** በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፡፡

ከሜዳዮች በተጨማሪ በረቂቅ **አዋጁ አንቀጽ 9 ላይ የኢትዮጵያ ታላቅ ክብር ኒሻን እና የአፍሪካ ታላቅ ክብር ኒሻን የሚባሉ ሁለት አይነት ኒሻኖች** ተቋቁመዋል፡፡

**የኢትዮጵያ ታላቅ ክብር ኒሻን** እንደ ሀገር ወይም በዓለም አቀፍ ደረጃ በአጠቃላይ በፖለቲካዉ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊ ዘርፎች እንዲሁም በዲፕሎማሲ መስክ እጅግ የላቀ አስተዋጽኦ ላበረከቱ ግለሰቦች፣ ቡድኖች ወይም ድርጅቶች የሚሰጥ ሲሆን የአፍረካ ታላቅ ክብር ኮከብ ኒሻን ደግሞ በልዩ ሁኔታ በአፍሪካ አህጉር ላለ ፖለቲካዊ፣ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊ ዘርፍ ችግርን የሚፈታ ስራ ለሰራ ወይም እንደ አህጉር በሀገራት መካከል መልካም ወዳጅነት እንዲዳብር እና ዘላቂ ትስስር እንዲፈጠር የሚያደርግ የላቀ ስራ ለሰራ ግለሰብ ቡድን ወይም ድርጅት የሚሰጥ ሽልማት ነዉ፡፡ ኒሻኖች በአብዛኛዉ ሀገራት ለሀገር መሪዎች እና በተመሳሳይ ደረጃ ላይ ለሚገኙ ግለሰቦች የሚበረከት ሽልማት ነዉ፡፡

ሜዳይ እና ኒሻኖችን ከላይ በተጠቀሰዉ አግባብ ጠቅለል ባሉ ዘርፎች ማቋቋም እና የሚሸለሙትንም አካላት ጠቅለል ባለ መልኩ ማስቀመጥ ያስፈለገበት በህግ አረቃቀቅ መርህ መሰረት አዋጅ መሰረታዊ የሆኑ ድንጋጌዎችን መያዝ ያለበት እና ዝርዝር ድንጋጌዎች በደንብ እና መመሪያ መደንገግ ያለባቸዉ በመሆኑ የላቀ አስተዋጽኦ ያበረከቱ

DANIEL FIKADU LAW OFFICE

**ግለሰቦች፣ ቡድኖች እና ድርጅቶች በተለያየ ዘርፍ ላይ የሚገኙ በመሆኑ በእያንዳንዱ የሙያ ዘርፍ የሚበረከተዉን ሜዳይ እና ኒሻን፤ እንዲሁም ለሽልማቱ ብቁ የሚሆኑ ግለሰብ፣ ቡድን እና ድርጅቶችን በአዋጁ ላይ ዘርዝሮ ማስቀመጥ ስለሚያስቸግር ነዉ፡፡** በመሆኑም በረቂቅ አዋጁ አንቀጽ 21(8) ላይ የጠቅላይ ሚኒስትር ጽ/ቤት የሜዳይ እና ኒሻን እጩ ተሸላሚዎችን በአዋጁ ከየተቀመጡት ዘርፎች የሚለዩበትን ዝርዝር የአፈጻጸም መመሪያ እንዲያወጣ ተደርጓል፡፡

በአዋጁ አንቀፅ 15 ላይ በአዋጅ ሜዳይን ፣ ኒሻንን እና ሽልማትን በተመለከተ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ክልሎች የራሳቸው የሽልማት ህግ ሊያወጡ እንደሚችሉ ተደንግጓል፡፡

ሌላዉ የሜዳይ እና ኒሻን ተሸላሚዎች ከሚሸለሙት ሜዳይ እና ኒሻን በተጨማሪ በማህበረሰቡ ዘንድ በዘላቂነት የሚታወሱበት እና ክብር የሚያገኙበት ሁኔታ ስለሚያስፈልግ በረቂቅ አዋጁ አንቀጽ 8 እና 12 ላይ ሊኖራቸዉ የሚገባ ልዩ መብቶች ተደንግገዉ ይገኛሉ፡፡ እንዲሁም በህገ-መንግስቱ መሰረት ሜዳይ፣ ኒሻን እና ሽልማት በሀገሪቱ ፕሬዝዳንት እንደሚሰጥ በተቀመጠዉ መሰረት በዚህ ረቂቅ አዋጅም ሜዳይ እና ኒሻን በፕሬዝዳንት እንደሚበረከት በግልጽ ተደንግጓል፡፡ በሌላ በኩል በሀገሪቱ በተለያዩ ዘርፎች ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያበረከቱ በርካታ ግለሰቦች፣ ቡድኖች እና ድርጅቶች ስለሚኖሩ እና ሁሉንም ሜዳይ እና ኒሻን መሸለም ከአቅም እና ከአፈጻጸም አንጻር ምቹነት ስለማይኖረዉ የተለያዩ የኢኮኖሚ፣ ማህበራዊ እና የአስተዳደር ዘርፎችን እና ሞያዎችን የተመለከቱ ሽልማቶችን ዘርፉን በሚመራው የሚኒስትር መስሪያ ቤት ምክረ ሃሳብ አቅራቢነት ብሔራዊ የሜዳይ እና ኒሻን ሽልማት ኮሚቴ በመመሪያ ሊያቋቁም የሚችልበት አግባብ በረቂቅ አዋጁ **አንቀጽ 14 ተደንግጓል።**

በረቂቅ አዋጁ አንቀጽ 18 ላይ ለሜዳይ እና ኒሻን ሽልማት ብቁ የሆኑ እጩዎችን እንደሀገር በመለየት ለጠቅላይ ሚኒስተሩ የሚያቀርብ አካል ስለሚያስፈልግ ብሔራዊ የሜዳይ እና ኒሻን ሽልማት ኮሚቴ በዚህ አዋጅ እንዲቋቋም ተደርጓል፡፡ ሰብሳቢዉን ጨምሮ የኮሚቴዉ አባላት በጠቅላይ ሚኒስትሩ እንዲሾሙ እና ተጠሪነታቸዉ ለጠቅላይ ሚኒስትሩ እንዲሆን ተደርጓል፡፡ በተጨማሪም በህገ-መንግስቱ አንቀጽ 74(10) ላይ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ኒሻኖችን እና ሽልማቶችን ለፕሬዝዳንት አቅርቦ እንደሚያሰጥ የተደነገገ በመሆኑ በረቂቅ አዋጁ አንቀጽ 19 ስር የጠቅላይ ሚኒስትር ጽ/ቤት እጩ ተሸላሚዎችን በተመለከተ ከኮሚቴዉ የሚቀርብ የዉሳኔ ሀሳብን የመጨረሻ ዉሳኔ እንዲሰጥበት ለጠቅላይ ሚኒስትሩ

የማቅረብ እና ሌሎች ከሜዳይ እና ኒሻን ሽልማት አስተዳደር ጋር የተያያዙ ስልጣን እና ተግባር እንዲፈጽም ሀላፊነት ተሰጥቶታል፡፡

በሌላ በኩል በህይወት ካሉ የሀገር ባለዉለታዎች በተጨማሪ አንዳንድ ግለሰቦች እጅግ የላቀ ስራ ለሀገር ሰርተዉ እዉቅና ሳያገኙ ህይወታቸዉ ያለፈ ስላሉ እነዚህን ግለሰቦች የሀገር ባለዉለታነታቸዉን ሊታወስ እና ክብር ሊሰጠዉ ስለሚገባ በልጆቻቸዉ ወይም በቤተሰቦቻቸዉ አማካኝነት የሜዳልያ ወይም የኒሻን ሽልማት የሚያገኙበት ስርዓት በረቂቅ አዋጁ አንቀጽ 22 ስር ተዘርግቷል፡፡ እንዲሁም ማንኛዉም ሜዳይ፣ኒሻን ወይም ሽልማት የተሸለመ ግለሰብ፣ ቡድን ወይም ድርጅት በህብረተሰቡ ዘንድ የሚሰጠዉ ክብር እና አመለካከት ከፍ ያለ ስለሚሆን ወይም እንደምሳሌ የሚታይ በመሆኑ ያልተገባ ተግባር ላይ ከመሳተፍ መጠንቀቅ ስለሚያስፈልግ በረቂቅ አዋጁ አንቀጽ 23 ስር ሜዳሊያዉ ወይም ኒሻኑ የተሸለመዉ በተሳሳተ ወይም በተጭበረበረ ማስረጃ ከሆነ ወይም ተሸላሚዉ ከአገር ክህደት ወንጀል ጋር በተያያዘ ወንጀል ጥፋተኛ ከተባለ የተሸለመዉ ሜዳይ፣ ኒሻን ወይም ሽልማትን እንደሚመልስ መደንገግ አስፈልጓል፡፡

ሌላዉ በረቂቅ አዋጁ አንቀጽ 27 ስር የተዘረዘሩ ጉዳዮች የተመለከተ ዝርዝር ድንጋጌ ማካተት የሚያስቸግር በመሆኑ ጉዳዮቹ ጠቅላይ ሚኒስትር ጽ/ቤት ይህን አዋጅ ለማስፈጸም በሚያወጣው መመሪያ እንዲወሰን ተደርጓል፡፡

## 5. ማጠቃለያ

በአጠቃላይ ይህ አዋጅ በህገ-መንግስቱ ሜዳይ፣ ኒሻን እና ሽልማት አሰጣጥን በተመለከተ የተቀመጠዉን እና ለረጅም ግዜ ማስፈጸሚያ ህግ ሳይወጣለት የቆየን ጉዳይ ወደ መሬት የሚያወርድ አዋጅ ነዉ፡፡ አዋጁ እስካሁን ድረስ በተበታተነ ሁኔታ ዝርዝር ማስፈጸሚያ ህግ ሳይወጣለት ሲከናወን የቆየዉን የሜዳይ፣ ኒሻን እና ሽልማት አሰጣጥ ህጋዊ ስርዓት የሚያበጅለት ሲሆን እንደ ሀገር፣ አህጉር እና ዓለም አቀፍ ደረጃ ትልቅ ስራ የሰሩ ግለሰቦች እና አካላትን ተገቢዉን እዉቅና እና ክብር በመስጠት በየትዉልዱ መነሳሳት እንዲፈጠር የሚያደርግ ህግ ነዉ፡፡

DANIEL FIKADU LAW OFFICE

# አዋጅ ቁጥር ---------/2016

# የኢትዮጵያ የሜዳይ፣ ኒሻን እና ሽልማት ረቂቅ አዋጅ

በሀገራችን በተለያዩ መስኮች የላቀ ስራ የሰሩ ግለሰቦችን እና ሌሎች አካላትን እዉቅና መስጠት ሌላው ማሕበረሰብ የነርሱን አርአያ እንዲከተሉ የሚያበረታታ፣የስራ ፈጠራ እንዲስፋፉ እና ሁለንተናዊ እና ቀጣይነት ያለዉ ልማት ለማስመዝገብ አስፈላጊ በመሆኑ፤

በፖለቲካ፣በዲፕሎማሲ፣በኢኮኖሚ እና በማህበራዊ ዘርፎች እንዲሁም በምርምር፣ በትህምርት፣በሳይንስና ቴክኖሎጂ፣በህክምና፣በስነ-ጥበብ፣በስነ ጽሁፍ፣ በባህል፣በአካባቢ ጥበቃ እና ሌሎች ተመሳሳይ ዘርፎች ለአገሪቱ እድገት ተጨባጭ የሆነና የላቀ ተግባር ለፈፀሙ ግለሰቦች፣ ቡድኖች እና ድርጅቶች ክብር እና እዉቅና መስጠት ተቀባይነት ያለዉ አሰራር በመሆኑ፤

በኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ 71(5) እና አንቀጽ 74(10) ላይ ኒሻን እና ሽልማትን በተመለከተ የተቀመጡት ድንጋጌዎችን የሚያስፈጽም እና በአጠቃላይ ሀገራዊ የሜዳይ ፣ኒሻን እና ሽልማት አሰጣጥ የሚመራበት ህጋዊ ሥርዓት መዘርጋት አስፈላጊ በመሆኑ፣

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲዊ ሪፐብሊክ ህገ-መንግስት አንቀጽ 55(1) መሰረት የሚከተለዉ ታዉጇል።

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

### 1. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ “የኢትዮጵያ የሜዳይ፣ ኒሻን እና ሽልማት አዋጅ ቁጥር -------/2016” ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

### 2. ትርጉም

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፡-

1/ **"የፈጠራ ስራ"** ማለት አግባብነት ባላቸዉ ህጎች የፓተንት ወይም የቅጂ እና ተዛማጅ መብት የተሰጠዉ የፈጠራ ስራ ነዉ፡፡

2/ **"ድርጅት"** ማለት ማንኛዉም የህግ የሰዉነት ያለዉ መንግስታዊ ወይም መንግስታዊ ያልሆነ ተቋም፣ወይም ዓለም አቀፍ ተቋም ነዉ፡፡

3/ **"የመንግስት ሰራተኛ"** ማለት በመንግስት መስርያ ቤቶች፣ በመንግስት ባለቤትነት በተያዙ የልማት ድርጅቶች ወይም በማናቸዉም መንግስት ባለቤት በሆነባቸዉ ተቋማት ዉስጥ ተመድቦ ወይም ተቀጥሮ የሚሰራ ሰዉ ነዉ፤

4/ **"ክልል"** ማለት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገ-መንግስት አንቀጽ 47 መሰረት የተቋቋመ ክልል ሲሆን የአዲስ አበባ እና ድሬደዋ ከተማ አስተዳደርን ይጨምራል፡፡

5/ ማንኛውም በወንድ ጾታ የተገለጸው የሴትንም ይጨምራል፡፡

## 3. የተፈፃሚነት ወሰን

ይህ አዋጅ ከወታደራዊ ወይም ከፖሊስ አገልግሎት ዉጪ በሆኑ በዚህ አዋጅ መሰረት ለሽልማት የሚያበቃ ተግባር በፈጸሙ ኢትዮጵያዉያን፣ ትዉልደ ኢትዮጵያዉያን ወይም የዉጭ ሀገር ዜጎች ወይም ድርጅቶች ላይ ተፈፃሚነት ይኖረዋል፡፡

# ክፍል ሁለት

# ስለሜዳዮችና ኒሻኖች መቋቋም እና የሚያስገኙት መብት

## 4. ስለ ሜዳዮች መቋቋም

የሚከተሉት ሜዳዮች በዚህ አዋጅ ተቋቁመዋል፡-

1/ ብሔራዊ የላቀ የፈጠራ ስራ ሜዳይ

2/ ብሔራዊ የህዳሴ ሜዳይ

3/ ብሔራዊ የላቀ ሲቪል አገልግሎት ሜዳይ

## 5. ብሔራዊ የላቀ የፈጠራ ስራ ሜዳይ

ብሔራዊ የላቀ የስራ ፈጠራ ሜዳይ በማናቸውም አይነት የፈጠራ ስራ በኢትዮጵያ ወይም በዓለም አቀፍ ደረጃ በተለያዩ ዘርፎች እጅግ የላቀ የህብረተሰብን ችግር የፈታ ወይም የሚፈታ የፈጠራ ስራ ለሰራ ግለሰብ፣ ቡድን ወይም ድርጅት ይሰጣል፡፡

## 6. ብሔራዊ የህዳሴ ሜዳይ

ብሔራዊ የህዳሴ ሜዳይ በሳይንስና ምርምር፣ በቴክኖሎጂ፣ በስነ-ጥበብ፣ በስፖርት ወይም በተለያዩ ዘርፎች ለሀገር፣ ለህዝብ ወይም በአጠቃላይ ለሰዉ ልጆች እጅግ የላቀ ስራ ለሰራ ግለሰብ፣ቡድን ወይም ድርጅት ይሰጣል፡፡

## 7. ብሔራዊ የላቀ ሲቪል አገልግሎት ሜዳይ

ብሔራዊ የላቀ ሲቪል አገልግሎት ሜዳይ በተመደበበት የመንግስት ስራ ስራዉ የሚጠይቀዉን ዲሲፕሊን ጠበቆ በታታሪነት እና በታማኝነት በማገልገል ለሀገር እና ህዝብ የላቀ ስራ ለሰራ ለመንግስት ሰራተኛ ይሰጣል፡፡

## 8. ሜዳይ ተሸላሚዎች ስለሚኖራቸዉ ልዩ መብቶች

በዚህ አዋጅ ከአንቀጽ (5)-(7) ድረስ የተደነገጉትን የሜዳይ አይነቶች የተሸለመ ግለሰብ ወይም ቡድን የሚከተሉት ልዩ መብቶች ይኖሩታል፡-

1/ ተሸላሚዉ ደሞዝ ካለዉ የደሞዙ ሃያ አምስት በመቶ (25%) ወይም ጡረተኛ ከሆነ የጡረታ አበሉ አርባ በመቶ (40%) ይጨመርለታል፤

2/ ተሸላሚዉ ደሞዝ ወይም ጡረታ ከሌለዉ ይህን አዋጅ ለማስፈጸም በሚወጣ መመሪያ የሚወሰን የገንዘብ መጠን በስጦታነት ይሰጠዋል፤

3/ በመንግስት የትምህርት ተቋሞች ቅድሚያ የትምህርት ዕድል ይሰጠዋል፤

4/ በመንግስት የጤና ተቋማት ነጻ የህክምና አገልግሎት ያገኛል፤

5/ በሀገሪቱ ፕሬዝዳንት የተፈረመ መታወቅያ እና ሰርተፊኬት ይሰጠዋል፡፡

## 9. ስለኒሻኖች መቋቋም

የሚከተሉት ኒሻኖች በዚህ አዋጅ ተቋቁመዋል፡-

1/ የኢትዮጵያ ታላቅ ክብር ኒሻን

2/ የአፍሪካ ታላቅ ክብር ኒሻን

## 10. የኢትዮጵያ ታላቅ ክብር ኒሻን

የኢትዮጵያ ታላቅ ክብር ኒሻን በኢትዮጵያ ወይም በዓለም አቀፍ ደረጃ በዲፕሎማሲ፣ በፖለቲካ፣ በኢኮኖሚ እና በማህበራዊ ዘርፎች ለሀገር እና ህዝብ እጅግ የላቀ ችግር ፈቺ ስራ ላበረከተ ግለሰብ፣ቡድን ወይም ድርጅት፤ ወይም ለኢትዮጵያ ልዩ ድጋፍ ላደረገ ሀገር ወይም የሀገር መሪ ይሰጣል፡፡

## 11. የአፍሪካ ታላቅ ክብር ኒሻን

የአፍሪካ ታላቅ ክብር ኒሻን ለአፍሪካ አህጉር በፖለቲካ፣ ኢኮኖሚ እና ማህበራዊ ዘርፎች አህጉራዊ ችግር ፈቺ ስራ ላበረከተ ወይም በአህጉሪቱ አገራት መካከል መልካም ወዳጅነት እና ዘላቂ ትስስር እንዲኖር ከፍተኛ አስተዋጽኦ ላበረከተ ግለሰብ፣ቡድን ወይም ድርጅት ይሰጣል፡፡

## 12. የኒሻን ተሸላሚ ስለሚኖረዉ ልዩ መብት

1/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 10 እና 11 መሰረት የኢትዮጵያ ወይም የአፍሪካ ታላቅ ክብር ኒሻን የተሸለመ ግለሰብ የሚከተሉት ልዩ መብቶች ይኖሩታል፡-

ሀ) ብሔራዊ በዓላት አከባበር ስነ-ስርዓት በሚከናወንበት ቀን እና ስፍራ በሚዘጋጅለት ቦታ ይቀመጣል፤

ለ) በስሙ መንገድ፣ ሆስፒታል፣ ትምህርት ቤት፤ ህንጻ ወይም ተመሳሳይ ተቋም ይሰየምለታል፤

ሐ) በሀገሪቱ ፕሬዝዳንት የተፈረመ መታወቂያ እና ሰርተፊኬት ይሰጠዋል

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ላይ ከተደነገጉት በተጨማሪ ኒሽን ተሸላሚዉ ኢትዮጵያዊ ወይም ትዉልደ ኢትዮጵያዊ ከሆነ የሚከተሉት ተጨማሪ ልዩ መብቶች ይኖሩታል፡-

ሀ) ተሸላሚዉ ደሞዝ ካለዉ የደሞዙ ሃያ አምስት በመቶ (25%) ወይም ጡረተኛ ከሆነ የጡረታ አበሉ አርባ በመቶ (40%) ይጨመርለታል፤

ለ) ተሸላሚዉ ደሞዝ ወይም ጡረታ ከሌለዉ ይህን አዋጅ ለማስፈጸም በሚወጣ መመሪያ የሚወሰን የገንዘብ መጠን በስጦታነት ይሰጠዋል፤

ሐ) በመንግስት የትምህርት ተቋሞች ቅድሚያ የትምህርት ዕድል ይሰጠዋል፤

መ) በመንግስት የጤና ተቋማት ነጻ የህክምና አገልግሎት ያገኛል፤

## ክፍል ሶስት

## ስለ ሜዳይ ወይም ኒሻን አሰጣጥ፣ ስለ ሽልማት እና ሀዉልት

### 13. ስለሜዳይ ወይም ኒሻን አሰጣጥ

1/ በዚህ አዋጅ መሰረት ሜዳይ ወይም ኒሻን ለመሸለም ብቁ የሆነ ግለሰብ፣ ቡድን ወይም ድርጅት በጠቅላይ ሚኒስትሩ አቅራቢነት ሽልማቱ በፕሬዝዳንት ይበረከትለታል፤

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገዉ እንደተጠበቀ ሆኖ የሜዳይ ወይም ኒሻን ሽልማት እንደሁኔታዉ ፕሬዝዳንቱ በወከለዉ ሰዉ ሊሰጥ ይችላል፤

### 14. ስለ ዘርፍ ሽልማቶች

ብሔራዊ የሜዳይ እና ኒሻን ሽልማት ኮሚቴ የተለያዩ የኢኮኖሚ፣ ማህበራዊ እና የአስተዳደር ዘርፎችን እና ሞያዎችን የተመለከቱ ሽልማቶችን ዘርፉን በሚመራው የሚኒስትር መስሪያ ቤት ምክረ ሃሳብ ሲያቀርብለት መርምሮ ውሳኔ ይሰጣል፡፡

### 15. የሽልማት አሰጣጥ በክልሎች

በዚህ አዋጅ ሜዳይን፣ ኒሻንን እና ሽልማትን በተመለከተ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ክልሎች የራሳቸው የሽልማት ህግ ሊያወጡ ይችላሉ፡፡

### 16. ሽልማት ስለሚበረከትላቸዉ ሰዎች ወይም አካላት

1/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 14 መሰረት የሚሸለሙ ሽልማቶች እንደየሽልማት ዘርፉ ከፍተኛ እና የሚያስመሰግን ስራ ለሰሩ የመንግስት ሰራተኞች፣ የመንግስት ሰራተኛ ላልሆኑ ግለሰቦች ወይም ድርጅቶች ይበረከታል፡፡

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሰረት የሚበረከት ሽልማት እንደየዘርፎቹ አይነት ዘርፎቹን በሚመሩ የመንግስት ተቋማት የሚሰጡ ይሆናል፤

3/ የሚበረከቱ ሽልማቶች አይነት እና መጠን፣ የተሸላሚዎች አመራረጥ እና ሌሎች ተያያዥ ጉዳዮች ይህን አዋጅ ለማስፈጸም በሚወጣ ደንብ/መመሪያ የሚወሰን ሆናል፤

## 17. ስለ ሀዉልት

1/ በዚህ አዋጅ መሰረት ሁለት ገዜ ወይም ከሁለት ግዜ በላይ ሜዳይ ወይም ኒሻን የተሸለመ ግለሰብ በማንኛዉም የሀገሪቱ አካባቢ አግባብነት ባለዉ ስፍራ ሀዉልት ሊቆምለት ይችላል፡፡

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሰረት የሚቆም ሀዉልት አይነት፣መጠን፣ ይዘት እና ሌሎች ዝርዝር ጉዳዮችን በተመለከተ በጠቅላይ ሚኒስትር ጽ/ቤት በሚወጣ መመሪያ የሚወሰን ይሆናል፡፡

# ክፍል አራት

# ስለብሔራዊ የሜዳይ እና ኒሻን ሽልማት ኮሚቴ እና ጠቅላይ ሚኒስትር ጽ/ቤት ተግባር እና ሀላፊነት

## 18. የሜዳይ እና ኒሻን ሽልማት ኮሚቴ እና ንዑሳን ኮሚቴዎች

1/ ብሔራዊ የሜዳይ እና ኒሻን ሽልማት ኮሚቴ (ከዚህ በኋላ "ኮሚቴ" እየተባለ የሚጠራ) በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፡፡

2/ የኮሚቴዉ ተጠሪነት ለጠቅላይ ሚኒስትሩ ይሆናል፡፡

3/ ኮሚቴዉ እንደአስፈላጊነቱ በስሩ የተለያዩ ንዑሳን ኮሚቴዎችን ሊያቋቁም ይችላል፡፡

## 19. የኮሚቴዉ አባላት

1/ ሰብሳቢውን ጨምሮ የኮሚቴዉ አባላት በጠቅላይ ሚኒስትሩ የሚሾሙ ይሆናል፡፡

2/ የጠቅላይ ሚኒስትር ጽህፈት ቤት ሀላፊ የኮሚቴዉ ፀሐፊ ይሆናል፡፡

## 20. የኮሚቴዉ ተግባር እና ሀላፊነት

ኮሚቴዉ የሚከተሉት ተግባራት እና ሀላፊነት ይኖሩታል፤

1/ በዚህ አዋጅ እና ይህን አዋጅ ለማስፈጸም በሚወጡ ደንብ እና መመሪያዎች መሰረት የሜዳይ እና ኒሻን ሽልማት የሚገባቸዉን እጩዎች ይመለምላል፣ ይመረምራል፣ ተገቢውን ውሳኔ ይሰጣል፤

2/ ለዉሳኔ እንዲረዳዉ እጩ ተሸላሚን በተመለከተ አስፈላጊ የሆነ የሰው ወይም የሰነድ ማስረጃ አስቀርቦ ይመራምራል፤

DANIEL FIKADU LAW OFFICE

3/ የሜዳይ ወይም የኒሻን ሽልማት የሚገባቸውን ግለሰቦች፣ቡድኖች ወይም ድርጅቶች ዝርዝር እና ይገባቸዋል የሚለው የሜዳይ ወይም ኒሻን አይነት ከነምክንያቱ የያዘ የዉሳኔ ሀሳብ ለጠቅላይ ሚኒስትሩ ያቀርባል፤

4/ የኮሚቴዉን የስራ ዘመን፣ የአሰራርና ስብሰባ ስነ-ስርዓት እና ሌሎች ተያያዥ ጉዳዮችን የሚወስን መመሪያ ያወጣል፡፡

## 21. የጠቅላይ ሚኒስትር ጽ/ቤት ስልጣን እና ተግባር

የጠቅላይ ሚኒስትር ጽ/ቤት የሚከተሉት ስልጣን እና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1/ ከኮሚቴ የሚቀርብ የዉሳኔ ሀሳብ የመጨረሻ ዉሳኔ እንዲሰጥበት ለጠቅላይ ሚኒስትሩ ያቀርባል፤ ጠቅላይ ሚኒስትሩ የቀረበዉን የዉሳኔ ሀሳብ መርምሮ ማጽደቅ፣ ማሻሻል፣ መሻር ወይም ሀሳቡ እንደገና ተጠንቶ እንዲቀርብ መመሪያ መስጠት ይችላል፤

2/ ኢትዮጵያዉያን ከዉጭ አገር መንግስታት የሚያገኟቸዉን ሜዳዮች ወይም ኒሻኖች በተሸላሚዎቹ ጥያቄ መሰረት፤ ወይም ለኢትዮጵያ መንግስት ወይም የመንግስት አካላት የተሰጡ ሜዳይ ወይም ኒሻኖች አግባብነታቸዉን በማየት ይመዘግባል፤

3/ በዚህ አዋጅ መሰረት ሜዳይ እና ኒሻን የተሸለሙትን ተሸላሚዎች ስም ወይም መረጃ መዝግቦ ይይዛል፤

4/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 23 መሰረት ሜዳይ ወይም ኒሻን መመለስ ካለባቸዉን ተሸላሚዎች ላይ ሽልማቱን ተከታትሎ ያስመልሳል፤ የመለሱ ተሸላሚዎችን ስም ወይም መረጃ መዝግቦ ይይዛል፤

5/ ሜዳይ እና ኒሻን ለተሰጣቸዉ ተሸላሚዎች በፕሬዝዳንት የተፈረመ የምስክር እና የመታወቂያ ወረቀት ይሰጣል፤

**6/** የሜዳይ እና ኒሻን ሽልማት የሚሰጥበትን ጊዜ ይወስናል፤ የሽልማት ዝግጅቱን ያቅዳል፤ ያስፈጽማል፤የተሸላሚዎችን ዝርዝር በይፋ በሚዲያ እንዲገለፅ ያደርጋል፡፡

7/ በዚህ አዋጅ መሰረት የተመሰረቱትን ሜዳዮች እና ኒሻኖች ያሰራል፣ መዝግቦ ይይዛል፤

8/ የሜዳይ እና ኒሻን እጩ ተሸለሚዎች የሚለዩበትን ዝርዝር የአፈጻጸም መመሪያ ያዘጋጃል::

9/ የአሸላለም ስነ ስርዓት ፕሮቶኮል መመሪያ ያወጣል፡፡

## ክፍል ስምስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### 22. ለሜዳይ፣ኒሻን ወይም ሽልማት የሚያበቃ ተግባር ፈጽሞ ስለሞተ ሰው

1/ በዚህ አዋጅ መሰረት ሜዳይ፣ኒሻን ወይም ሽልማት ለማግኘት የሚያበቃ ተግባር ፈጽሞ የሞተ ሰው አግባብነት ያለው ሜዳይ፣ኒሻን ወይም ሽልማት ይዘጋጃል፤ በስሙ ይመዘገባል፤

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሰረት የተዘጋጀ ሜዳይ፣ኒሻን ወይም ሽልማት ለሟቹ ተሸላሚ ታላቅ ልጅ ወይም በልጆቹ እድሜ ቅደም ተከተል መሰረት የሚሰጥ ይሆናል።

3/ ሟቹ ተሸላሚ ልጅ ከሌለው ለባለቤቱ፤ ባለቤት ከሌለው አግባብ ባለው የውርስ ሕግ መሰረት ለውርስ ባለመብቱ ሽልማቱ ይሰጣል፤

4/ የሟቹ ተሸላሚ ልጆች ለአቅመ አዳም ያልደረሱ ከሆነ አግባብነት ባለዉ ህግ የልጆቹ ሞግዚት ወይም አሳዳጊ ለሆነ ሰዉ ሽልማቱን ይረከባል፤

5/ ሟቹ ተሸላሚ የጡረታ አበል ካለዉ አግባብት ባለው ሕግ የጡረታ አበል ተጠቃሚ ለሆነ ሰዉ የጡረታ አበል ጭማሪ ይደረግለታል።

### 23. ሜዳይ፣ኒሻን ወይም ሽልማትን መልሶ ስለመውሰድ

1/ በዚህ አዋጅ መሰረት የተሰጠ ማንኛዉም ሜዳይ፣ኒሻን ወይም ሽልማትን በሚከተሉት ምክንያቶች ተሸላሚዉ መመለስ አለበት፡-

ሀ) አግባብነት ባለው ህግ የሚኖረው ተጠያቂነት እንደተጠበቀ ሆኖ ሜዳዩ፣ ኒሻኑ ወይም ሽልማቱ በተሳሳተ ወይም በተጭበረበረ ማስረጃ ላይ ተመስርቶ የተሰጠ ሲሆን፤

ለ) ተሸላሚዉ አግባብነት ባለዉ ህግ በጽኑ እስራት የሚያስቀጣ ከአገር ክህደት ጋር የተያያዘ ወንጀል ፈጽሞ ጥፋተኛ ከተባለ፤

2/ በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ 1 አግባብ ሜዳይ፣ ኒሻን ወይም ሽልማት የሚመልስ ሰዉ በዚህ አዋጅ መሰረት ያገኛቸዉ ልዩ መብቶች እንደ አስፈላጊነቱ ቀሪ ሲሆኑ ወይም ሊታገዱ ይችላሉ።

### 24. የመተባበር ግዴታ

ማንኛውም ሰው ይህን አዋጅ በማስፈጸም ረገድ ከሚመለከተው አካላት ጋር የመተባበር ግዴታ አለበት።

DANIEL FIKADU LAW OFFICE

## 25. ቅጣት

1/ ማንኛውም ሰው አግባብነት ካለዉ አካል ፍቃድ ሳያገኝ በዚህ አዋጅ የተመለከቱትን ሜዳይ፣ ኒሻን እና ሽልማት ያዘጋጀ ወይም ወደ ሐሰት የለወጠ እንደሆነ ከሦስት ዓመት በማይበልጥ እስራት ወይም ከአስር ሺህ ብር በማይበልጥ የገንዘብ መቀጮ ወይም እንደነገሩ ሁኔታ በሁለቱም ይቀጣል፡፡

2/ ማንኛውም ሰው ሳይፈቀድለት ኒሻን አድርጎ ከተገኘ ከስድስት ወር በማይበልጥ ቀላል እስራት ወይም ከአምስት ሺህ ብር በማይበልጥ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል፡፡

## 26. ተፈፃሚነት ስለማይኖራቸው ሕጎች

ከዚህ አዋጅ ጋር የሚቃረን አዋጅ፣ ደንብ፣መመሪያ ወይም ልማዳዊ አሰራር በዚህ አዋጅ በተሸፈኑ ጉዳይዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም፡፡

## 27. በመመሪያ የሚወሰኑ ጉዳዮች

የሚከተሉት ጉዳዮች ጠቅላይ ሚኒስትር ጽ/ቤት በሚያዘጋጀዉ መመሪያ ይወሰናል፡-

1/ በዚህ አዋጅ መሰረት የሚሸለሙ ሜዳዮች እና ኒሻኖች ይዘት፣ቅርጽ እና መጠንን፤

2/ ሜዳይ እና ኒሻን የሚሸለሙ ሰዎች/ድረጅቶች ቁጥር ብዛት፤

3/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 14 መሰረት የሚበረከቱ ሽልማቶች አይነት እና መጠን፤

4/ ስለ ሜዳይ እና ኒሻን አደራረግ እና አቀማመጥ፡፡

## 28. ደንብና መመሪያ የማውጣት ሥልጣን

1/ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ይህን አዋጅ ለማስፈፀም ደንብ  ሊያወጣ ይችላል፤

2/ የጠቅላይ ሚኒስትር ጽ/ቤት ይህን አዋጅ እና አዋጁን ለማሰፈጸም የሚወጣ ደንብን ለማስፈጸም መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፤

## 29. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ.........ቀን....../2016 ዓ.ም**
**ሳሕለወርቅ ዘዉዴ**
**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክሪያሲያዊ**

**ሪፐብሊክ ፕሬዝዳንት**

DANIEL FIKADU LAW OFFICE

## Proclamation No……./2023

## Ethiopian Medal, Nishan and Award Proclamation

Whereas, it is important to acknowledge persons and other organs who have done Excellent/outstanding works in the different sectors so as to encourage a society to follow their leads; growing of inventions/innovations; and bring inclusive and consistent development;

Whereas, it is an acceptable task to honor and acknowledge persons, groups and organizations who have done an outstanding and concrete works for the development of the country in political, diplomacy, economic and social sectors; as well as in Researches, Education, Science and Technology, Medicine, Art, Literature, Culture, Environmental Protection and other similar sectors;

Whereas, it is necessary to establish a legal system which generally governs awarding of national Medal, Nishan and Prizes and that also implements article 71(5) and 74(10) of the constitution which deal about Nishan and awards;

Now therefore, in accordance with Article 55(1) of the Federal Democratic Republic of Ethiopia constitution it is hereby proclaimed as follows.

## PART ONE

## GENERAL PROVISIONS

1. **Short Title**

   This proclamation may be cited as "Ethiopian Medal, Nishan and Award Proclamation No…. /2023"

2. **Defnition**

   In this Proclamation, unless the context otherwise requires: -

   1/ **"Innovation"** means an innovation work which is granted a patent or copyright right according to relevant laws.

   2/ **"Organization"** means a Governmental or Non-Governmental Institution;or International Institution which has acquired legal personality.

3/ **"Government Employee"** means a person who is employed or appointed in government institutions (offices), State owned enterprises or any organs which is owned by Government.

4/ **"Region"** means a state recognized under Article 47 of the constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia.

5/ Any expression in the masculine gender includes feminine gender

**3. Scope of Application**

This proclamation applies on all Ethiopians, Ethiopian Origins, Foreign nationals or Organizations, except persons who serve in military and police services,

## PART TWO

## ESTABLISHMENT OF MEDALS AND NISHANS; AND THEIR PRIVILAGES

**4. Establishment of Medals**

The following Medals are established according to this Proclamation: -

1/ National Outstanding Innovation Medal;

2/ National Renaissance Medal;

3/ National Outstanding Civil Service Medal.

**5. National Outstanding Innovation Medal**

National Outstanding Invention/Innovation/Entrepreneurship Medal is awarded to an Individual, Group or Organization who has done any outstanding innovation on various sectors which solves or will solve Social or Economic problems of a society at Ethiopian or International level.

**6. National Renaissance Medal**

National Renaissance Medal is awarded to an Individual, Group or Organizations who has done an outstanding work for the society or all human beings as a general, in science and research, technology, Art, Sport or various sectors.

7. **National Outstanding Civil Service Medal**

National Outstanding Civil service Medal is awarded to government employee who has done an outstanding work for the nation and the public by maintaining the discipline of the work he is assigned with diligently and loyally.

8. **Privileges of Medal Award Receivers**

An individual or Group who is awarded a Medal according to Article (5)-(7) of this proclamation has the following rights:-

1/ If the awardee has a salary or is a pension receiver, he shall get an incremental of twenty five percent (25%) of the salary or forty percent (40%) of the pension payment;

2/ If the awardee has no salary or pension payment, he shall get an amount of money as a gift that is determined by the directive issued to implement this proclamation;

3/ Gets priority of education opportunity at government educational institutions;

4/ Gets free medical services at government health facilities;

5/ Gets an identification card and certificate signed by the president of the country.

9. **Establishment of Nishans**

The following Nishans are established pursuant to this proclamation:-

1/ Great Honor Nishan of Ethiopia

2/ Great Honor Nishan of Africa

10. **Great Honor Nishan of Ethiopia**

Great Honor Nishan of Ethiopia is awarded to an Individual, Group or Organization that has contributed an outstanding work for the nation and the public that can solve problems in diplomacy, politics, economic or social sector; or it is awarded to a country or leader who has given special support for Ethiopia.

11. **Great Honor Nishan of Africa**

Great Honor Nishan of Africa is awarded to an Individual, Group or Organization that has contributed an outstanding work for Africa that solves continental problems in the political, economic or social sectors of the African continent or has made a significant contribution to good friendship and consistent partnership between countries of the continent.

DANIEL FIKADU LAW OFFICE

**12. Privilages of Nishan Award Receivers**

1/ A person who is awarded Great Honor Nishan of Africa, as per Article 10 and 11 of this proclamation, has the following Privileges:-

(a) Sits at a place prepared for him on the national holidays celebration place and date;

(b) Naming of Road, Hospital, School, Building or similar institution in his;

(c) Gets an identification card and certificate signed by the president of the country.

2/ In addition to those stated on sub Article 1 of this article, if the awardee is an Ethiopian or Ethiopian origin, he has the following Privileges:-

(a) If the awardee has a salary or is a pension receiver, he shall get an incremental of twenty five percent (25%) of the salary or forty (40%) of the pension payment;

(b) If the awardee has no salary or pension payment, he shall get an amount of money as a gift that is determined by the directive issued to implement this proclamation;

(c) Gets priority of education opportunity at government educational institutions;

(d) Gets free medical services at government health facilities;

## PART THREE

## AWARDING OF MEDAL AND NISHANS; ABOUT PRIZES AND STATUE

**13. Awarding of Medals and Nishans**

1/ A person, Group or an Organization that is eligible to be awarded a Medal or Nishan according to this proclamation, up on the recommendation of the Prime Minister, will receive the award from the President.

2/ Subject to the provisions of sub-article 1 of this article, the award of Medal or Nishan may be given by the person assigned by President as the case may be;

**14. Establishment of Prizes**

A Prize pertaining to various social, economic and administrative sectors and professions is issued by the National Medals, Nishans and Awards Committee on the basis of proposals for the establishment of such Prizes to be submitted to the Committee by the respective Ministries overseeing the sectors.

**15. Prize awarding by the Regions**

Notwithstanding the provisions of this proclamation, regarding the Medals, Nishans and prizes regions may enact their own prize laws

**16. Persons or Entities to whom the award is given**

1/ Prizes established in accordance with Article 14 of this Proclamation shall be given to public servant, non-public servant or organization which has performed high and commendable work on the prize fields.

2/ The prizes given pursuant to sub Article 1 of this Article, in accordance with the type of the prizes, shall be given by the government institutions that lead the sectors;

3/ The type and amount of prizes, the selection of prize receivers and other related issues will be determined by the regulations/directive issued to implement this proclamation.

**17. STATUTE**

1/ A statue may be erected in any appropriate place in the country for a person who has been awarded a medal or Nishan twice or more than twice in accordance with this proclamation.

2/ The type, size, content and other details of the statute to be erected according to sub Article1 of this Article is determined by a directive issued by the Prime Minister's Office.

**PART FOUR**

## DUTIES AND RESPONSIBILITIES OF THE NATIONAL MEDAL AND NISHAN AWARD COMMITTEE AND THE PRIME MINISTER'S OFFICE

**18. . Medal and Nishan Award Committee and Sub-Committees**

1/ The National Medal and Nishan Award Committee (hereinafter referred to as "The Committee") is hereby established by this Proclamation.

2/ The committee will be accountable to the Prime Minister.

3/ The committee may establish various sub-committees under it as may be necessary.

**19. Members of the Committee**

1/ The members of the committee, including the chairman, shall be appointed by the Prime Minister.

2/ The head of the Prime Minister's office shall be the secretary of the committee.

**20. Duties and Responsibilities of the Committee**

The Committee has the following Duties and Responsibilities:-

1/ In accordance with this Proclamation; and the regulations and directives issued to implement this Proclamation, it recruits, examines and makes appropriate decisions on candidates who deserve the Medal and Nishan Awards;

2/ Examines witness and documentary evidences, regarding candidates of the award, to reach on decision;

3/ Submits recommendation to the Prime Minister with a list of individuals, groups or organizations deserving of Medal or Nishan awards and the type of Medal or Nishan they deserve, along with the reasons;

4/ Issues a directive that determine the working period, Working and meeting procedure of the committee and other related issues.

**21. Duties and Responsibilities of the Prime Minister's Office**

The Prime Minister's Office has the following Duties and Responsibilities:-

1/ Submits a recommendation of the committee to the Prime Minister for a final decision; The Prime Minister may examine and approve, amend, revoke or give instructions for the recommendation to be re-examined;

2/ Considering their relevance, records medals and Nishans that Ethiopians receive from foreign governments up on the request of the awardees; or medals and Nishans awarded to Ethiopian government or government officials.

3/ Records the names or information of the awardees who have been awarded Medals and Nishans in accordance with this Proclamation;

4/ Receives back awards from the awardee who shall return back Medal and Nishan as per article 23 of this Proclamation; records the names or information of returning awardees;

5/ Gives a certificate and an Identification card, signed by the President, to the awardees who have been awarded Medal and Nishan;

6/ Determines the timing of award of Medal and Nishan; Plans the awards ceremony; executes; discloses the list of awardees publicly by the media.

7/ Prepares and records the Medals and Nishans established in accordance with this Proclamation;

8/ Issues directive to identify nominees for Medal and Nishan.

9/ issues a protocol for the ceremony of the award

## PART FIVE

## MISLANEOUS PROVISIONS

**22. Persons died of doing an act resulting in a Medal, Nishan or Prize Awards**

1/ A relevant Medal, Nishan or Prize shall be prepared for deceased person eligible of receiving a Medal, Nishan or Prize according to this proclamation; the award will be registered in his name.

2/ A medal, Nishan or Prize prepared according to sub Article 1 of this article will be given to the eldest child of the deceased recipient or according to the next age order.

3/ If the deceased recipient has no children, to his wife and if there is no wife, the award will be given to his successor according to the relevant law of succession;

4/ If the deceased recipient's children have not reached the age of majority, the award will be handed over to a person who is the guardian of the children according to the relevant law;

5/ If the deceased recipient has a pension, the pension will be increased to a person who is a pension receiver under the relevant law.

**23. Taking Back a Medal, Nishan or Prize**

1. Any Medal, Nishan or Prize awarded pursuant to this Proclamation shall be returned by the awardee for the following reasons:-

A/ Subject to liability under the relevant law, where the medal, Nishan or prize is awarded based on false or fraudulent evidence;

B/ If the awardee has been convicted of a crime that relates with treason & punishable by imprisonment under the relevant law;

2/ Special rights of a person who returns Medal, Nishan or Prize according to sub article 1 of this article may be avoided or cancelled as the case may be.

**24. Duty to Cooperate**

Everyone has a duty to cooperate with the relevant authorities in the implementation of this Proclamation.

**25. Punishment**

1/ Any person without obtaining permission from the relevant body, prepares or falsify a Medal, Nishan or Prize referred in this Proclamation shall be punishable with an imprisonment not exceeding three years or a fine not exceeding ten thousand birr or with both as the case may be.

2/ Any person found wearing a Medal or Nishan without permission, shall be punishable with simple imprisonment not exceeding six months or a fine not exceeding five thousand birr.

**26. Inapplicable Laws**

Any Proclamation, Regulation, Directive or Practice inconsistent with this Proclamation shall not apply to the matters covered by this Proclamation.

**27. Matters to be determined by Directive**

The following matters shall be determined by the directive prepared by the Prime Minister's Office:-

1/ Content, shape and size of Medals and Nishans to be awarded in accordance with this Proclamation;

2/ The number of Medal and Nishan awardees;

3/ Type and amount of prizes to be awarded in accordance with Article 14 of this Proclamation;

DANIEL FIKADU LAW OFFICE

4/ The arrangement and placement of Medal and Nishan.

**28. Power to issue regulations and Directives**

1/ The Council of Ministers may issue regulations to implement this Proclamation;

2/ The Prime Minister's Office may issue directive for the implementation of this Proclamation and regulations issued to implement the Proclamation;

29. **Effective Date**

This Proclamation shall be effective from the date of its publication on the Federal Negarit Gazette.

**Addis Ababa………/2023**

**Sahlework Zewde**

**President of the Federal Democratic Republic of Ethiopia**